# የግላዊነት መግቢያ

ተሳታፊዎች የየራሳቸውን ግላዊ የግላዊነት ስሜት እና በሕይወታቸው ላይ የሚኖረውን ተጽዕኖ ይፈትሻሉ። ተሳታፊዎች በግላቸው መያዝ የሚፈልጉዋቸውን የመረጃ አይነቶች እና አንዳንድ መረጃዎችን ይፋ የሚያደርጉባቸው/የማያደርጉባቸው ዐውዶችን ይመርምራሉ።

# ማቴርያሎች

የግላዊነት ጨዋታ የሚታደል ጽሁፍን

# "ግላዊነት" ለእርስዎ ምን ማለት ነው?

## የግላዊነት ጨዋታ

**የክላስ መስተጋብር**

የግላዊነት ጨዋታ የሚታደል ጽሁፍን ያሰራጩ። **ለተማሪዎችዎ ይንገሩዋቸው**

ሁልጊዜ ስለ በግላዊነትዎ ላይ ውሳኔ ያሳልፋሉ፣ በተለይም ወደ መስመር በሚወጡ እና ሞባይል ወይም ሌሎች መሳሪያዎችዎን በሚጠቀሙ ጊዜ። ብዙውን ጊዜ፣ ስለ እነዚህ ውሳኔዎች በማሰብ ብዙ ጊዜ አያጠፉ ይሆናል። ነገር ግን ሁሉም ተደማምረው የእርስዎ ልዩ የግላዊነት አረዳድ ይሆናሉ።

ግላዊነት ማለት ሌሎች ሰዎች ስለ እርስዎ የሚያውቁትን ነገር የመቆጣጠር ችሎታ ማለት ነው። ይህን ስለ እርስዎ የተወሰኑ ነገሮችን በመናገር ይፈጽሙታል (ለምሳሌ ለሌሎች ሰዎች አድራሻዎን ወይም ዘና ለማለት ምን ማድረግ እንደሚያስደስትዎ) ወይም ነገሮችን ሌሎች ሰዎች ባሉበት በማድረግ (ለምሳሌ ከጓደኞች ጋር ወደ መደብር መሄድ እና የሚፈልጓቸውን ነገሮች መምረጥ)። ከሌሎች ሰዎች ጋር በአንድ ክፍል ውስጥ ቢሆኑም ወይም ከእነርሱ ጋር በመስመር ላይ የሚያወሩም ቢሆን ግላዊነት አስፈላጊ ነው።

ግላዊነት በራስዎ ውሳኔ የሚመሰረት ነው። ግላዊነት ለእርስዎ ወይም ለቤተሰብዎ የሚሰጠው ትርጉም በዚህ ቡድን ውስጥ ላሉ ሰዎች እና ቤተሰቦቻቸው ከሚሰጠው ትርጉም የተለየ ሊሆን ይችላል። እኛ የግል ነው ብለን ዋጋ የምንሰጠውን ነገርን እና በመስመር ላይ የሚኖረን ጠባይ እንዴት ግላዊነታችን ላይ ተጽዕኖ እንደሚኖረው የምናውቅ ከሆነ፣ ምን አይነት ግላዊነት እንደምንፈልግ የተሻሉ ምርጫዎችን ለመውሰድ እንችላለን።

አሁን እርስዎ ስለ ግላዊነት እንዴት እንደሚያስቡ እና ምን እንደሚሰማዎ እንዲያዩ የሚረዳዎ ግላዊነትን የሚመለከት አጭር ጌም [እባክዎ የግላዊነት ጌም ደብተር ይመልከቱ] ላይ እንሳተፋለን። የሚታደለውን ጽሁፍዎን ይሞላሉ፣ ይዘውት በክፍሉ ዙሪያ ይራመዳሉ፣ እና እራስዎን ለሌላ ተሳታፊ ያስተዋውቃሉ። እርስዎ እና ሌላው ተሳታፊ ከዚያም እርስ በራሳችሁ በታደለው ጽሁፍ ላይ ስላለው መረጃ ጥያቄ ትጠያየቃላችሁ። ደብተሩ ራሱ ለሌላ ተሳታፊ አያሳዩ! ደብተርዎ ስራውን ከጨረሱ በኋላ አይወሰድብዎትም— ከፈለጉ ወደቤትዎ ይዘዉት ይሄዳሉ ካልፈለጉ ደግሞ ሊወረውሩት ይችላሉ።

በእያንዳንዱ ውይይት፣ እያንዳንዱ ተሳታፊ ሌላኛው ተሳታፊ ለሚያቀርባቸው እያንዳንዳቸው ጥያቄዎች ቢያንስ ሶስት መልሶችን ማጋራት አለበት። ተሳታፊዎች ከሶስት በላይ መልሶችን ማጋራት

ይችላሉ። ተሳታፊዎች በተጨማሪም የትኞቹን ሶስት ወይም ከዚያ በላይ መረጃ ማጋራት እንዳለባቸው መምረጥ ይችላሉ። እያንዳንዱ ተሳታፊ ምን ያህል መረጃ ያጋራል? እያንዳንዱ ተሳታፊ የትኛውን መረጃ ያጋራል? እንራመድ እና እናውራ!

**የክላስ መስተጋብር**

ተሳታፊዎች የሚታደለውን ጽሁፍ እንዲሞሉ ያድርጉ። ከዚያም ተሳታፊዎች በክፍሉ ዙሪያ እንዲንቀሳቀሱ እና እርስ በራሳቸው እንዲነጋገሩ 15 ደቂቃ ይስጧቸው። ከዚያም በኋላ፣ የሚከተሉትን ጥያቄዎች በመጠቀም ከመላው ቡድን ጋር ውይይት ይያዙ። በመጨረሻም፣ ተሳታፊዎች የሚታደለውን ጽሁፍ እንዲጥሉት ወይም ይዘውት እንዲሄዱ ያድርጉ - እንደ አስተማሪ ወረቀቶቹን አይሰብስቡ።

## ውይይት

***ተማሪዎችዎን ይጠይቁ***

ለማንም ሰው ያላጋሯቸው ነገሮች ነበሩ? የትኞቹ ናቸው? ለምን?

የትኞቹን ነገሮች አጋሩ? ለምን?

የትኛውን ነገር ማጋራት እንዳለበት ተመሳሳይ ውሳኔ የወሰደ ሰው ነበር? ለምን / ለምን አልሆነም?

በሚያጋሩት ሰው ላይ ተመስርቶ፣ የዚህን አይነት መረጃ ከዚህ በላይ ወይም በታች ሊያጋሩ የሚችሉበት ምክንያት ምን ይሆን ነበር? መቼ ያጋሩት ነበር?

እርስዎ ለሚያውቁት ለማንኛውም ሰው ሊያጋሩት የማይችሉት የነበረ ግን በዚህ መልመጃ ውስጥ ያጋሩት ነገር አለ? ለምን አልሆነም?

የዚህ አይነት መረጃ ይፋዊ ነው? ግላዊ ነው? ለምን? ይህ ለሁሉም ሰው እንደዚያው ነው?

***ለተማሪዎችዎ ይንገሩዋቸው***

እንደሰሙት፣ ሰዎች የትኛውን መረጃ ማጋራት እና የትኛውን ደግሞ አለማጋራት እንዳለባቸው የተለያዩ ውሳኔዎችን ወስደዋል። በተጨማሪም ለወሰዷቸው ውሳኔዎች የተለያዩ ምክንያቶች አሏቸው።

አሁን ያደረግነው ጨዋታ ነበር። ነገር ግን እነዚህኑ አይነት ውሳኔዎች በየቀኑ በእውነተኛው ሕይወታችን ውስጥ እንወስዳለን። አንድን ፎቶ በማኅበራዊ ሚዲያ ላይ መለጠፍ ይኖርብን ወይም አይኖርብን እንደሆነ እንወስናለን። አንድ የተወሰነ የመገኛ መረጃ፣ ለምሳሌ ኢሜይል አድራሻ፣ በማኅበራዊ ሚዲያ ውስጥ ለሕዝብ ይፋ እንዲሆን የምንፈልግ ስለመሆኑ እንወስናለን። አሁን የምንወስነው፣ የቅርብ ጓደኞችን

ከሚወስነው ወይም እኛ ራሳችን ባለፈው ወር ከወሰንነው ሊለይ ይችላል። በተለያዩ ጊዜዎች ተመሳሳይ ውሳኔ ብንወስን እንኳን ምክንያቶቻችን የተለያዩ ሊሆኑ ይችላሉ።

እነዚህ የተለያዩ ውሳኔዎች እና ምክንያቶች የእኛን የግላዊነት ግላዊ አረዳድ ይወክላሉ።

በቀላሉ ሲቀመጥ፣ ግላዊነት፣ ስለ እኛ የሚገልጥን መረጃ እንዴት እንደምንይዝ የምንወስደውን ምርጫን ያመለክታል። ይህ መረጃ የእኛን ማንነት፣ እንቅስቃሴ፣ ምርጫዎች፣ የዕለት ተዕለት እንቅስቃሴዎች፣ እና ሌሎችንም የሕይወታችንን ገጽታዎች በከፊል ያካትታል። በዛሬው ዲጂታል ዓለም፣ ስለራሳችን መረጃ ለሌሎች ለማጋራት ከመቼውም ጊዜ በላይ ዕድሎች አሉ። ስለዚህ ስለራሳችን ግላዊነት ያለንን አረዳድ መረዳት እና ያ አረዳድ ጥሩ ስሜት የሚፈጥርልን ስለመሆኑ ማወቅ አስፈላጊ ነው።

***ተማሪዎችዎን ይጠይቁ***

በጨዋታው ውስጥ ባሳዩት ጠባይ መሰረት እና በዕለት ተዕለት ኑሮዎ ውስጥ በሚኖረዎ ጠባይ፣ ግላዊነትን እንዴት ይገልጹታል? ለምን?

ሁሉም ግላዊ መረጃ ምስጢርም ጭምር ነው?

1. የግድ አይደለም። ለምሳሌ፣ የዲያሪ ጽሁፎችዎ የሆኑትን ያህል የልደት ቀንዎ ምስጢር ላይሆን ይችላል። በዓለም ላይ የልደት ቀንዎን የሚያውቁ እና ማወቅ ያሚያስፈልጋቸው ብዙ ሰዎች አሉ፣ ለምሳሌ ወላጆችዎ / አሳዳጊዎችዎ ወይም ሐኪምዎ። ነገር ግን፣ አንድ ነገር ምስጢር ባይሆንም፣ እንደ ግላዊ መረጃ ሊገነዘቡት ይችላሉ። ብዙዎቻችን ሁሉም ሰው የልደት ቀናችንን እንዲያውቅ አንፈልግም ምክንያቱም ያ መረጃ ለእኛ ቅርብ የሆኑ እና ለማወቅ ልዩ ምክንያት ያላቸው

ሰዎች ብቻ ሊያውቁት የሚገባ መረጃ እንደሆነ ስለምናስብ ነው። አንድን ነገር ስለ እኛ ማወቅ የሚገባው ማን እንደሆነ፣ መቼ እና ለምን የመሳሰሉ ውሳኔዎች የግላዊነት ቁልፍ ናቸው።

***ተማሪዎችዎን ይጠይቁ***

የግድ ምስጢር ያልሆኑ ነገር ግን ለማያውቋቸው ወይም ገና አሁን ለተዋወቋቸው ሰዎች የማያጋሯቸው ሌሎች ነገሮች አሉ?

1. ስልክ ቁጥሮች፣ ኢሜይሎች፣ ፎቶዎች፣ ቪዲዮዎች፣ ወዘተ።

ከወላጆችዎ / አሳዳጊዎችዎ ወይም ጓደኞችዎ የሚደብቋቸው ነገሮች አሉ? መምህራን እና ሌሎች አስተማሪዎችስ?

1. የትምህርት ቤት ውጤትዎ፣ የInstagram መለያዎ፣ ዲያሪዎ።

ስለራስዎ የግላዊነት አረዳድ አስገራሚ የሆነብዎ የተማሩት ነገር አለ?

***ለተማሪዎችዎ ይንገሩዋቸው***

ከጨረስን በኋላ የግላዊነት ጨዋታውን ይዘውት መሄድ ይችላሉ። አሁን ስለ ግላዊነት የበለጠ እያሰቡ ነው፣ የራስዎን የግላዊነት አረዳድ ወደ ድርጊት የሚቀይሩባቸው በየቀኑ ውሳኔ ለመወሰን በርካታ ዕድሎችን ያያሉ።

# ምድብ ሥራ

## ምድብ ሥራ

### ለተማሪዎችዎ ይንገሩዋቸው

አሁን የእርስዎ ስለ ግላዊነት ያለዎትን ግላዊ አረዳድ እንመረምራለን።

1. በመስመር ላይ አንድ ሰው ያጋራው ወይም የለጠፈው እርስዎ ቢሆኑ ግን ይፋ የማያወጧቸው ሶስት ነገሮችን ያግኙ። ይህ ከታዋቂ ሰዎች፣ የፖለቲካ ሰዎች፣ ወይም የንግድ ሥራ መሪዎች ሊሆን ይችላል፣ ወይም በሃሽታግ ወይም ማናቸውንም ምሳሌዎች ለማግኘት መደበኛ ፍለጋ ሊፈልጉት ይችላሉ። የተለያዩ ምንጮችን ለማግኘት ይሞክሩ (ለምሳሌ፣ ፎቶዎች፣ በጽሁፍ ላይ የተመሰረቱ ልጥፎች፣ ለምሳሌ አንድ ሰው በማኅበራዊ ሚዲያ ወይም የዜና ሚዲያ ላይ ስለተለያዩ ርዕሶች የለጠፋቸው አስተያየቶች)።
2. ለእያንዳንዱ ምሳሌ፣ ይህን እርስዎ ቢሆኑ ለምን ይፋ እንደማያደርጉት የሚያስረዳ ባለ አንድ አንቀጽ ማብራሪያ ይጻፉ። በአንቀጽዎ ውስጥ፣ እባክዎ ይህን ይዘት በማጋራት ላይ ያለዎ አመለካከት እንደ ዐውዱ ሁኔታ ሊቀየር ይችል እንደሆነ ያስረዱ (ለምሳሌ:- እያወሩት ያሉት ሰው፣ በውይይቱ ላይ የተሳተፉ ሰዎች ቁጥር፣ አላማ እና ግብ፣ አካባቢ [ትምህርት ቤት ወይም ከትምህርት ቤት ውጭ])።

**ምድብ ስራ**

ተሳታፊዎች ሥራውን እንዲጨርሱ 40 ደቂቃ ይስጧቸው።

ይህ መማሪያ ነገር በ Berkman Klein Center for Internet &amp ላይ በወጣት እና ሚድያ የቀረበ ነው; ሃርቫርድ ዩኒቨርስቲ ሶሳይቲ በ Creative Commons Attribution-ShareAlike 4.0 International ፈቃድ ስር። ወጣት እና ሚድያን እንደ ኦርጂናል ምንጭ እስከጠቀሱ እና ተጨማሪ ስራዎችን በተመሳሳይ ስምምነት መሰረት እስካከናወኑ ድረስ ከሱ የተወሰዱ ንግዳዊም ንግዳዊ ያልሆኑም ከሱ የተወሰዱ ነገሮች መጠቀም ይችላሉ። እነዚህን እና ተጨማሪ መማሪያ ነገሮችም Berkman Klein's Digital Literacy Resource Platform መስመር ላይ ይገኛሉ።